መመሪያ ቁጥር **20 /2006** *ዓ.ም*

<u>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጤና ተቋማት ደረጃ ለሚያገለግሉ የጤና ሙያተኞች የተረኝነትና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ</u>

በወቅቱ ከሚታየው የአገልግሎት ፈላጊው ህዝብ ብዛትና ይኸው ከሚፈጥረው የሥራ ጫና አንፃር የጤና ሙያተኞች ኃላፊነትና ግዴታቸውን በሙሉ ተነሳሽነት ሊወጡ የሚችሉበትንና ተረጋግተው የሚሠሩበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ፤

በተለይም በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ደረጃ የሚያገለግሉ የጤና ሙያተኞች ካለባቸው የበሽታ ወይም የአደጋ ተጋላጭነት አንፃር ሲደረግላቸው የቆየው የእስካሁን የማበረታቻ ክፍያ እንደመልካም ጅምር የሚቆጠር ቢሆንም ከሁኔታዎችና ከወቅቱ የገበያ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ተጨማሪ ማሻሻያ እንዲደረግበት በተደጋጋሚ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በህገር ደረጃ ተጠንቶ የቀረበዉን የትርፍ ጊዜ አበልና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ከክልሉ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ /58/ ንዑስ አንቀጽ /7/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል ።

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ደረጃ /በጤና ተቋማት/ ለሚያገለግሉ የጤና ሙያተኞች የተረኝነትና የኃላፊነት አበል መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር ---/2006 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፣

1. **"**የተረኝነት አበል" ማለት ከመንግሥት መደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በሌሊት ፣ በበዓላት ወይም የልዩ በዓላት ቀን በሆስፒታል ወይም በጤና ጣቢያ ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ለተመደበ የጤና ሙያተኛ እንዲከፈል በዚህ መመሪያ የተወሰነው የአበል ዓይነት ነው።
2. **"**ተረኝነት" ማለት ማናቸውም የክልሉ መንግሥት ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ የ 24 ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት ይቻለው ዘንድ የተለያየ ዝግጅት ያላቸው የጤና ሙያተኞች ን፮ግራም እየወጣላቸው መደበኛ ከሆነው የመንግሥት ሥራ ሠዓት ውጭ ህብረተሰቡን እንዲያገለግሉ የሚደረግበት ሥርዓት ነው።
3. "ተረኛ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ሥር በተመለከተው ሥርዓት የሚመራ ማንኛውም የጤና ሙያተኛ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ ሠጭ ሠራተኞችን ሊጨምር ይችላል ።
4. **"**ኦን ዲዊቲ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ተረኛ ሆኖ እንዲያገለግል የተመደበ የጤና ሙያተኛ በተረኝነት እንዲሠራ በተመደበባቸው ሰዓታት ሁሉ በአንድ ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ ውስጥ ሙሉ ጊዜውን አገልግሎት እንዲሰጥ የሚገደድበት አሠራር ነው።
5. **"**ኦን ኮል" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በተረኝነት እንዲያገለግል የተመደበ የጤና ሙያተኛ ሙሉ ጊዜውን በሆስፒታሉ ወይም በጤና ጣቢያው ቅጥር ግቢ ማሳለፍ ሳያስፈልገው የእሱ ልዩ እገዛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ካለበት አካባቢ እየተጠራ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚደረግበት አሠራር ነው ።

6. **“**የኃላፊነት አበል” ማለት በሆስፒታሎች ወይም በጤና ጣቢያዎች ውስጥ በኃላፊነት ተመድበው የሚሠሩ የጤና ሙያተኞች ለሚሰጡት የጤና ሥራ አመራርና ለሚያበረክቱት ሙያዊ አስተዋጽኦ በዚህ መመሪያ ተወስኖ የሚከፈላቸው የአበል አይነት ነው ።

3. ዓላማዎች

መመሪያው ከዚህ በታች የተመለከቱት ዓላማዎች ይኖሩታል ።

1. የጤና ሙያተኞችና ረዳት ሠራተኞች ተነቃቅተውና ተረጋግተው እንዲሠሩ ማስቻል ፣
2. ለጎ/ሰቡ ጥራቱን የጠበቀና የተቀላጠፈ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበትን ስልት ውጤታማ ማድረግ ፣
3. በመስኩ ያለውን ውስን የሰው ኃይል ባግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
4. በጤና ተቋማት ዘንድ የሚታየውን የተለያየ የትርፍ ጊዜ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች አከፋፈል ለማስወገድና የመልካም አስተዳደር ችግርን ለማቃለል ፣

4. የተፈፃሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሆስፒታሎችና ወረዳዎች በሚያስተዳድሯቸው ጤና ጣቢያዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ።

5. የተረኝነትና የኃላፊነት አበል ተሻሽሎ የተወሰነ ስለመሆኑ፤

በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ደረጃ የሚያገለግሉ የጤና ሙያተኞችና ረዳቶቻቸው የተረኝነትና የኃላፊነት አበል በዚህ መመሪያ መሠረት እንደገና እንዲሻሻል ተወስኗል ። የተሻሻለውን የተረኝነትና የኃላፊነት አበል መጠንና የሙያ ዓይነት ወይም የኃላፊነት ደረጃ የሚያመለክቱት ሠንጠረዦች የመመሪያው ክፍልና አካል ተደርገው ዕዝል 1 እና ዕዝል 2 በመሆን ተያይዘዋል ።

6. የተረኝነት አበል ስለሚከፈልባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሠረት የተረኝነት አበል ሊከፈል የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይሆናል ፦-

1. የሶስት ሽፍት ስርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የማይቻልበት ተጨባጭ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ ማለትም የተተኪ ባለሙያ መታጣት ወይም የሙያተኛ እጥረት የሚታይበት ዘርፍ መኖር ፤

2. በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ መሰጠቱ ሊቋረጥ የማይችል የጤና አገልግሎት መኖር፣
3. በህዝብ በዓላት ቀን ወይም ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ወጭ በተረኝነት መሠጠት ያለበት የጤና አገልግሎት ወይም መፈፀም የሚገባው ኘሮግራም የመኖሩ አጋጣሚ ፣

7. በኃላፊነት ስለሚከፈል የአበል አከፋፈል፤

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የኃላፊነት አበል የሚከፈላቸው ሙያተኞች በኃላፊነት የተመደቡት ብቻ ይሆናሉ ።
2. በዚህ መመሪያ መሰረት የኃላፊነት አበል የሚከፈላቸዉ ሙያተኞች ከዚህ በፊት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናቱ ወይም በስራ አመራር ቦርድ ፀድቀዉ ተግባራዊ የሆኑ እና ወደፊት በቢሮዉ እየተጠኑ የሚወሰኑ የኃላፊነት ቦታዎች ይሆናሉ።
3. ለዚህ ምደባ የሚያበቁት መመዘኛዎች በጤና ተቋማት ተጠንተው እስኪሻሻሉ ድረስ በስራ ላይ ያሉት መስፈርቶች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል ።
4. የኃላፊዎች አመዳደብ ምደባ በስራ አመራር ቦርድ /በጤና ጣቢያ አመራር ኮምቴ እየቀረበ ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል።

8. የተፈቀዱ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች /አበሎች/፤

8.1. አዲሱ የተረኝነት አበል ፤

- የቀን የተረኝነት አበል = የተሰራ የትርፍ ሰዓት ብዛት X በ 1 ሰዓት ደመወዝ ተባዝቶ፤
- የተጠባባቂ ተረኝነት አበል= የተረኝነት አበል መጠንን በ 30% / ተጠባባቂ ተረኝነት ተመድቦ ካልተፈለገ/ ይከፈላል።

8.2. <u>እጥረት ያለባቸው ሙያተኞች አበል፤</u>

–

በዚህ የሙያ አበል ውስጥ የተካተቱት ክሊኒካል ስፔሻሊስቶችና ጠቅላላ ሀኪሞች ሲሆኑ በየጤና ተቋማቱ ማለትም በሪፈራል፣ ዞናልና ገጠር ሆስፒታል ለተመደቡ፤

- ክሊኒካል ስፔሻሊስቶች ብር 2000.00 ብር እና
- ለጠቅላላ ሀኪሞች(GP) ብር 1000.00 በየወሩ ልዩ የሙያ አበል ተፈቅዷል፤

8.3. <u>የመኖሪያ ቤት ማካካሻ አበል፤</u>

- ይህ አበል ለክሊኒካል ስፔሻሊስቶች ና ጠቅላላ ሀኪሞች በየወሩ ብር ***1000*** የቤት ኪራይ ተፈቅዷል፤

8.4. <u>የተጋላጭነት ክፍያ አበል፤</u>

8.4.1. ዝርዝራቸዉ ከዚህ ቀጥሎ ለተመለከቱት ሙያዎች በወር **470** የተጋላጭነት ክፍያ የተፈቀደላቸዉ፤

- አዋላጅ ነርስ፤
- ሰመመን ነርስ፤
- አዕምሮ ህክምና ነርስ፤
- የራጅ ተከኒሽያን፤
- የድንገተኛ ህክምና ፓራሜዲካል፤
- ጨረርና ኒዉክለር ህክምና ዉስጥ የሚሰሩ መካከለኛ ባለሙያዎች፤

8.4.2. ዝርዝራቸዉ ከዚህ ቀጥሎ ለተመለከቱ ሙያዎች በወር ብር **1225** የተጋላጭነት አበል የተፈቀደላቸዉ፤

- የቀዶ ጥገና፤
- የማህጸን ጽንስ ሀኪም፤
- አጥንት ሀኪም፤
- የተቀናጀ ድንገተኛ ቀዶ ጥገናና ጽንስ ህክምና ኦፊሰር፤
- የድንገተኛ ህክምና ስፔሻሊስት፤
- የድንገተኛ ህክምና መኮነን፤
- ክሊኒካል ፓቶሎጂስት እና
- ኦንኮሎጂ /ጨረር ህክምና የሚሰራ/

9. <u>የአመራርነት ማትጊያ አበል፤</u>

ተ.ቁ	ኃላፊነት	የመ/ደረጃ ሆስፒታል	አጠቃላይ ሆስፒታል	ሪፈራል ሆስፒታል	ምርመራ
1	ዋና ስራ አስኪያጅ	900	1200	1500	
2	ሜዲካል ዳይሬክተር	700	1000	1300	
3	የዋና ስራ ክፍል ኃላፊ የዉስጥ ደዌ፤ የቀዶ ጥገና፤ የማህፀን ጽንስ ፤ የህጻናት ህክምና.. ወዘተ/	500	700	900	
4	ሜትረን	400	600	800	
	ም/ረዳት ሜትረን	300	400	650	
	የስራ ክፍል ኃላፊ	200	300	350	
	ሌሎች የአገልግሎት ክፍሎች አስተባባሪዎች/ ምሳሌ የራጅ/ የላቦራቶሪና ፋርማሲ ክፍል/	200	300	350	
5	የሪጅናል ላቦራቶሪ ማዕከል ኃላፊ			900	አዲስ
6	የጤና ጣቢያ ኃላፊ			800	የተወሰነ/በክልል

10. የተረኝነት አገልግሎት ከኃላፊነት ጋር ስላለዉ ግኙኝት፤

1. የኃላፊነት አበል የሚያገኙ ሜትረኖችና ነርሶች በተረኝነት ተመድበው በዲዊቲ የሚሰሩ ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ዕረፍት አይሰጣቸውም
2. በተረኝነት ተመድቦ ዲዊቲ ያደረ ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ከሰዓት በፊት ብቻ እንዲያርፍ ይፈቀድለታል ።

11. በኦን ኮል /በተጠባባቂነት/ ስለሚመደቡ የጤና ሙያተኞች መብትና ግዴታ፤

1. በኦን ኮል እንዲያገለግሉ የሚመደቡ የጤና ሙያተኞች በህዝብ በዓላት ቀንና ቅዳሜና እሁድ በኦንኮል ሲመደቡ በዚህ መመሪያ መሠረት ሙሉ የተረኝነት አበል ይከፈላቸዋል ሆኖም በሥራ ቀን በሚመደቡበት ጊዜና ተጠባባቂ ሁኖ ተመድቦ ካልተፈለገ 30% ይከፈለዋል፤ ሙሉ የተረኝነት አገልግሎት ከሠጠ ሙሉ ይከፈለዋል።
2. በኦንኮል የሚመደቡ የጤና ሙያተኞች በተመደቡበት ቀን ለአገልግሎቱ ቢጠሩም ባይጠሩም በጤና ተቋሙ ተገኝተው በመታከም ላይ ያሉ ወይም አዲስ በመግባት ላይ ያሉ ህሙማን መኖራቸውን የተረዱ እንደሆነ በሚመለከተው ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ በአካል በመገኘት ህሙማኑን መጐብኘት ይኖርባቸዋል ።

12. በተረኝነት ስለመመደብ፤

1. ማንኛውም የጤና ሙያተኛ በተረኝነት እንዲሠራ የሚመደበው ለ 15 ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል።
2. በልዩ ሁኔታ ከፍ ብሎ በአንቀጽ 12 /1/ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ በመ/ቤቱ ኃላፊ ዉሳኔ በተጨማሪ እንዲሠራ ከተደረገ ግን በሥራው ሰዓት ልክ እየታሰበ የተረኝነት አበል ክፍያው ሊፈፀም ይችላል።
3. ሙያተኞች የተረኝነት አበል ክፍያ የሚያገኙት የሰሩበት ሰዓት አባሪ ሁኖ በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት በሚመለከተው የክፍል ኃላፊ ተሞልቶ /ተመዝግቦ/ በኬዝ ማናጀሮች እየተረጋገጠ በሜዲካል ዳይሬክተር ቀርቦ ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል ።

13. በምትክ ሙያተኞች ስለመገልገል፤

1. የፋርማሲ ባለሙያ በሌለበት የጤና ድርጅት ከሊኒካል ነርሶችንና ጤና ረዳቶችን እንደአስፈላጊነቱ በተረኝነት መድቦ ማሠራት ይቻላል ። የአበል ክፍያው ልክ ግን ለሙያቸው የተቀመጠውን ደረጃ የተከተለ ይሆናል ።
2. በዞንና በገጠር ሆስፒታል እንዲሁም የጽንስና ማህፀን ወይም የቀዶ ህክምና ስፔሻሊስቶች ባልተመደቡበት በማናቸውም ሌላ ሆስፒታል ወይም ተመድበውም በተለያዩ ምክንያቶች በቦታው በማይገኙበት ጊዜ የድንገተኛና ቀዶ ህክምና ጽንስ ህክምና ኦፊሰሮች ተክቶ ማሠራት ይቻላል ።

14. የአበል ክፍያው ከግብር ነፃ ስለመሆኑ፤

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከፈል የተረኝነትም ሆነ የኃላፊነት አበል የሥራ ግብር አይከፈልበትም ።

15. ኃላፊነትና ተጠያቂነት

1. በተረኝነትም ሆነ በኃላፊነት አበል ስም ከዚህ መመሪያ ውጭ ለሙያተኞች የሚፈፀም ማናቸውም ክፍያ ህጋዊ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ይሆናል ።
2. ማንኛዉም በተረኝነት የተመደበ ባለሙያ በተመደበበት ቦታ የመገኘት ፤ በተረኝነት ከተመደበ በኋላ አቋርጦ መዋፋት፤ በክፍሉ ዉስጥ የመኝታ አልጋ ማስገባት ክልክል ነዉ።
3. የትርፍ ጊዜ ክፍያዉ ሰዓት ደቂቃ መሰረት ያደረገ በመሆኑ በተረኝነት የተመደበ ኃላፊ ወይም ባለሙያ በተቋሙ ከተገኘበት / ከሰራበት ጊዜ በላይ ክፍያ ጠይቆ የወሰደ ባለሙያ ፤የመዘገበ ያረጋገጠ ኃላፊ በስነ- ምግባር ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።
4. ተደጋጋሚ /ከ 3 ጊዜ በላይ / የደንበኛ ቅሬታ የቀረበበት በተረኝነት የተመደበ ባለሙያ በተረኝነት እንዳይመደብ ሊወሰኑና በዲስፕሊን መመሪያ መሰረት መጠየቅ ይኖርበታል።

16. ስለ ተቋማት ሥልጣን፤

1. በዚህ መመሪያ ከፀደቀዉ የሰዉ ኃይል ተጨማሪ የሚያስፈልግ ሁኖ ከተገኘ የጤና ድርጅቶች የየአካባቢያቸውን የታካሚ ብዛትና ይኸው የሚያስከትለውን የሥራ ጫና መጠን መሠረት በማድረግ የሚያሰማሯቸውን ተረኛ ሙያተኞች ቁጥርና እንዲህ ሊመቻችለት የሚገባውን አገልግሎትና የሚያስፈልገዉን የሙያ ዓይነት በየጊዜው እያሻሻሉ በሆስፒታል ስራ አመራር ቦርድና በጤና ጣቢያ ስራ አመራር ኮምቴ አማካኝነት የመወሰን ስልጣን የኖራቸዋል ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም የዚህ መመሪያ አባሪዎች በሆኑት ሠንጠረዦች ከተመለከቱት ሙያተኞች ቁጥርና የተወሰኑ የሙያ ዓይነቶች ውጭ በየትኛውም ተቋም ውስጥ በተረኝነትም ሆነ በኃላፊነት መድቦ ማሠራትና የአበል ክፍያ መፈፀም የሚቻለው ለጤና ጣቢያ የወረዳ አስተዳዳሪዉን ፤ በሆስፒታሎች ደረጃ የጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊዉን የቅድሚያ ስምምነት ማግኘት ሲቻል ብቻ ነዉ።

17. የተሻሩ መመሪያዎች፤

ከዚህ በፊት የተላለፉ የኃላፊነትና የትርፍ ሰዓት አበል አከፋፈል መወሰኛ መመሪያዎች ደብዳቤዎች ተሽረው በዚህ የተሻሻለ መመሪያ ተተክተዋል ።

18. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሀሴ 9 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ባህር ዳር

ነሀሴ 9 ቀን 2006 ዓ.ም ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል

መስተዳድር ምክር ቤት

ዕዝል 1

የአመራርነት ማትጊያ አበል

1. ሪፈራል የሆስፒታል

ተ/ቁ	የሙያ አይነት	የተፈቀደ አበል በወር	የባለሙያ ብዛት	ምርመራ
1	ዋና ሥራ አስኪያጅ	1500.00	1	
2	ሜዲካል ዳይሬክተር	1300.00	1	
3	**ዋና ሥራ ክፍል ኃላፊ ኬዝማኔጀር**			
3.1	የድንገተኛ ሕክምና ኬዝማኔጀር ክፍል ኃላፊ	900.00	1	
3.2	የማህፀንና ጽንስ ኬዝ ማኔጀር ክፍል ኃላፊ	900.00	1	
3.3	የተኝቶ ታካሚ ኬዝ ማኔጀር ክፍል ኃላፊ	900.00	1	
3.4	የተመላላሽ ሕክምና ኬዝ ማኔጅር ክፍል ኃላፊ	900.00	1	
4	**የሥራ ክፍል ኃላፊ/ አስተባባሪ/**			
4.1	የውስጥ ደዌ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.2	የቀዶ ጥገና ተኝቶ ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.3	የድንገተኛ ታካሚ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.4	የትራያጅና ተመላላሽ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.5	ጋይኒ/የማህፀንና ጽንስ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.6	የማተርኒቲ /ማዋለጃ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.7	የግብዓት/ፋርማሲ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.8	የላቦራቶሪ ኪዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
4.9	የቀዶ ጥገና (OR) ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5	ቲቢ/ኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.1	የአይን ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.2	የ X-Ray/ራጅ/ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.3	የጥርስ ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.4	የስነ አእምሮ ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.5	የአጥንት ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.6	የእናቶችና ሕፃናት(M.C.H)ኬዝቲም አስተባባሪ	700.00	1	
5.7	የህፃናትና ተኝቶ ሕክምና ኬዝቲም አስባባሪ	700.00	1	
6	ሜትረን	800.00	1	
7	ረዳት ሜትረን	650.00	1	

2. ዞናል ሆስፒታል

ተ/ቁ	የሙያ አይነት	የተፈቀደ አበል በወር	የባለሙያ ብዛት	ምርመራ
1	ዋና ሥራ አስኪያጅ	1200.00	1	
2	ሜዲካል ዳይሬክተር	1000.00	1	
3	**ዋና ሥራ ክፍል ኃላፊ ኬዝማኔጀር**			

3.1	የድንገተኛ ሕክምና ኬዝማኔጀር	700.00	1	
3.2	የማህፀንና ጽንስ ኬዝ ማኔጀር	700.00	1	
3.3	የተኝቶ ታካሚ ኬዝ ማኔጀር	700.00	1	
3.4	የተመላላሽ ሕክምና ኬዝ ማኔጅር	700.00	1	
4	**የሥራ ክፍል ኃላፊ/ አስተባባሪ/**			
4.1	የውስጥ ደዌ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.2	የቀዶ ጥገና ተኝቶ ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.3	የድንገተኛ ታካሚ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.4	የትራያጅና ተመላላሽ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.5	ጋይኒ/የማህፀንና ጽንስ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.6	የማተርኒቲ /ማዋለጃ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.7	የሕብዓት/ፋርማሲ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.8	የላቦራቶሪ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.9	የቀዶ ጥገና (OR) ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.10	የእናቶችና ሕፃናት(M.C.H)ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.11	የአይን ሕክምና ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.12	የ X-Ray/ራጅ/ ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.13	የማገገሚያ (ICU) ኬዝቲም አስተባባሪ	500.00	1	
4.14	የህፃናትና ተኝቶ ሕክምና ኬዝቲም አስባባሪ	500.00	1	
5	**ሜትረን**	600.00	1	
6	**ረዳት ሜትረን**	400.00	1	

3. ገጠር ሆስፒታል

ተ/ቁ	የሙያ አይነት	የተፈቀደ አበል በወር	የባለሙያ ብዛት	ምርመራ

1	ዋና ሥራ አስኪያጅ	900.00	1	
2	ሜዲካል ዳይሬክተር	700.00	1	
3	**ዋና ሥራ ክፍል ኃላፊ ኬዝማኔጀር**			
3.1	የድንገተኛ ሕክምና ኬዝማኔጀር	500.00	1	
3.2	የማህፀንና ጽንስ ኬዝ ማኔጀር	500.00	1	
3.3	የተኝቶ ታካሚ ኬዝ ማኔጀር	500.00	1	
3.4	የተመላላሽ ሕክምና ኬዝ ማኔጅር	500.00	1	
4	**የሥራ ክፍል ኃላፊ/ አስተባባሪ/**			
4.1	የግብዓት/ፋርማሲ ኬዝቲም አስተባባሪ	200.00	1	
4.2	የላቦራቶሪ ኬዝቲም አስተባባሪ	200.00	1	
5	**ሜትረን**	400.00	1	

ዕዝል- 2

<u>በተረኝነት የሚመደብ ባለሙያ ብዛት</u>

ተ.ቁ	የባለሙያ ዓይነት	በተረኝነት የሚመደብ ባለሙያ ብዛት				
		ጤና ጣቢያ	የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል	ጠቅላላ ሆስፒታል	ሪፈራል ታስፒታል	ምርመራ
1	የዉስጥ ደዌ ስፔሻሊስት			0.3	1	

2	የህጻናት ህክምና ሰፔሻሊስት			0.3	1	
3	የጸንስና የማህጸን ህክምና ሰፔሻሊስት			1	2	
4	የቀዶ ጥጋና ህክምና ሰፔሻሊስት			1	2	
5	የአጥንትህክምና ሰንፔሻሊስት			1	1	
6	የአይን ህክምና ሰንፔሻሊስት			0.3	1	
7	የተቀናጀ ቀዶ ጥገና ኦፊሰር		1			
8	ጠቅላላ ሃኪም		1	2	12	
9	ጤና መኮንን	0.3				
10	የሰመመን ባለሙያ		1	1	3	
11	ነርስ ፕሮፌሽናል		1	3	6	
12	ጠቅላላ ነርስ	1	4	8	19	
12	ሚድዋይፍ	1	2	3	5	
13	ፋርማሲስተ			1	2	
14	ድራጊስት	0.3	1	1	2	
15	ላብራቶሪ ቴክኖሎጅስት			1	2	
16	ላብራቶሪ ቴክኒሽያን	0.3	1	1	2	
17	ራዲዮግራፈር		1	1	2	
18	ራዲዮቴክኖሎጅስት					ያልተቀመጠ
19	ድጋፍ ሰጭ ሰራተኛ					
	ድምር	3	13	26	63	